# የማይተላለፍ የዝሆኔ በሽታን አስመልክቶ የተዛቡ አስተሳሰቦችን እንለዉጥ



የማይተላለፍ ዝሆኔ እንደ ማንኛውም ዓይነት በሽታ ነው። በሃጥያት ምክንያት ወይንም ደግሞ በፈጣሪ ቁጣ የሚከሰት ህመም አይደለም።



የማይተላለፍ የዝሆኔ በሽታ በጊዜ እና በወቅቱ ካልታከምነው ለከፋና ረጅም ጊዜ ለሚቆይ ስቃይ ይዳርገናል። በበሽታዉ ተጠቂ ነኝ ብለህ/ብለሽ ካሰብክ/ካሰብሽ በአስቸኳይ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ተገቢ የሆነ ህክምና ማግኘት ያስፈልጋል። በሽታው በቅድሚያ ከታወቀ እና ከታከመ ከሚያስከትለው ውስብስብ ችግር መከላከል ይቻላል።



ከማይተላለፍ የዝሆኔ በሽታ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ተገቢውን ክትትልና ህክምና ካደረጉ መደበኛ እና ውጤታማ የሆነ የሕይወት ኑሮ መምራት ይችላሉ።



የማይተላለፍ ዝሆኔ እንደማንኛው በሽታ ህመም ነው። ስለዚህ በበሽታው የተጠቁ ታማሚዎችን እንደግፋቸው፤ የሚደርስባቸውንም መገለል እናስቁም!



የማይተላለፍ የዝሆኔ በሽታ ማንኛውንም የህብረተሰብ ክፍል ሊያጠቃ ይችላል። ስለሆነም ማኛውንም ሰው ባለበት የጤና ችግር ምክንያት ያለምንም ልዩነት መንከባከብ ይገባል።



የማይተላለፍ የዝሆኔ በሽታ ማንነተህን/ሽን እንዲወስን አትፍቀድለት /አትፍቀጂለት። አንተ/አንቺ ዋጋ ያለህ/ያለሽ አንዱ የማህበረሰብ ክፍል ነህ/ነሽ። ስለሆነም ተገቢ የሆነ አክብሮት ይገባሃል/ይገባሻል።

OSSREA
5S FOUNDATION
FUNDED BY NIHR National Institute for Health Research
UKaid from the British people